የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ—ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 5
ADDIS ABABA–6th December, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፱/፲፱፻፺፬ ዓ.ም.
ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፮፻፵፰

## CONTENTS

Proclamation No. 259/2001
Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Addis Ababa International Airport Project Additional Loan Ratification Proclamation ........................ Page 1648

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፱/፲፱፻፺፬

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፫ ቀን ፪ሺ፩ በካይሮ የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም ዓቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፱/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 259/2001

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

WHEREAS, a Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of Three Million United States Dollars (USD. 3,000,000) for financing the Addis Ababa International Airport Project (Additional Loan), was signed in Cairo, on the 3rd day of May, 2001;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 6th day of December, 2001;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Addis Ababa International Airport Project (Additional Loan) Ratification Proclamation No.259/2001."

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፫ ቀን ፪ሺ፩ በካይሮ የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው ፡፡

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሦስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (፫ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ፡፡

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed in Cairo on the 3rd day of May, 2001, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of Three Million United States Dollars (USD. 3,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of December, 2001.

Done at Addis Ababa, this 6th day of December, 2001.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE